# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ህዳር 5/ 2000 ዓም

## መግለጫ

### በወያኔ እጅ የወደቁት ጀግኖች ጓዶች በእኛ አይረሱም

ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በወያኔ የጭካኔ ይዞታ የወደቁት የኢሕአፓ ታጋይ ጓዶች እስከዛሬ ድረስ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ በትክክል ማወቅ የቻለ ሰውም ሆነ ተቋም አልተገኘም። መዳረሻቸውን ለማወቅ የተደረገው ማነኛውም ጥረትና ድካም ሁሉ አንዳችም ውጤት ሊያስገኝልን ከቶ አልቻለም። በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅቶችም ይሁን በእኛ በራሳችን በኩል የተካሄደው ፍለጋና ውጣ ውረድ ሁሉ ስኬታማ ሊሆን አልቻለም። በኢሕአፓ ላይ ይህ ነው የማይባል ጥላቻና ፍርሃት የተጠናወታቸው የወያኔ መሪዎች፥ በእነኝህ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቁርጥ ቀን ታጋይ ጓዶቻችን ላይ ይህን ያህል አረመኒያዊ ድርጊት ማድረጋቸው፥ ወይም ደግሞ የት እንዳደረሷቸው እንኳ ለመግለጽ አለመድፈራቸው፥ መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ የቱን ያህል ቂመኛና በቀለኛ መሆናቸውን ከመግለጹ በቀር የእነርሱን የሰብእና ማንነት በትክክል የሚገልጽ ነው።

ጀግኖች ጓዶቻችን በአመኑበት ዓላማ ጸንተው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከመታገልና ከመሰቃየት ባሻገር፤ ቅንጣት ያህል ወንጀል አልሰሩም። ይህንን ያህል ዘመን የት እዳደረሷቸው ባለመግለጻቸው፥ የወያኔ መሪዎች፥ በህግም፥ በታሪክም፥ በኢትዮጵያ ሕዝብም፥ ዘንድ ተጠያቂዎች ይሆናሉ። ይህን ብሔራዊ ወንጀል ትውልድ ይረሳዋል ተብሎም የሚጠበቅ አይሆንም።

ዕርግጥ ይህ በትግራይ ሕዝብ ስም ሲታገል የነበረው የመለስ ዜናዊ ዘረኛና አሸባሪ ቡድን፥ ለአለፉት 17 ስድስት ዓመታት የመንግሥት ሥልጣን በኃይል ከጨበጠ አንስቶ፥ ዕልፍ አዕላፍ ሰላማዊ ዜጎችን እንደ ጨፈጨፈ፥ እንዳሰረና እንዳሰደደ መላው ዓለም የሚያውቀው ሃቅ ከሆነ ቆይቷል። የኢሕአፓም ታጋይ ጓዶቻችን እጣና ፈንታ ከእነዚህ እልፍ አዕላፍ ወገኖቻችን ሁኔታ ተለይቶ እንደማይታይ እንረዳለን። ተይዘው ደብዛቸው የጠፋው ጓዶችን ጠቅላላ ሁኔታ የተለየ ሊያደርገው የሚችለው፥ ከአለፉት ሃያ ዓመታት በላይ ጀምሮ፥ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ በህይወት ይኑሩ አይኑሩ አለመታወቁ ነው። በተለይ ለጓዶቻቸው፤ ለቤተሰቦቻቸውና ለቅርብ ዘመዶቻቸው ይህ ነው የማይባልና ያልተቋረጠ የኅሊና ሰቀቀን እንደሆነም መገመት የሚያስቸግር አይደለም።

ለተሰዋ ጀግና አክብሮትና አድናቆት እያበረከቱ ሕይወትን መቀጠል የእኛ የኢትዮጵያውያን የባኅላችን መግለጫ ዓይነተኛ ታሪካችን በመሆኑ፥ እነዚህ በአረመኔዎቹ የወያኔ መሪዎች እጅ ወድቀው መዳረሻቸው የት እንደሆነ ያልታወቁትን ጓዶቻችንን የመጨረሻ ሁኔታ ባለማወቃችን እንደ እግር እሳት ከሚያቃጥሉን ሌሎች ብሔራዊ ጥቃቶችና ሀዘኖች መካከል ግንባር ቀደሙን ቦታ ይዟል። ኢሕአፓ እንደ ድርጅት፥ በዓላማቸው ፀንተው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገቡትን የትግል ቃል ኪዳን አክብረው ለተሰዉ፥ ለተሰቃዩና በዕስር ቤት ዕነበለ- ፍርድ ለሚማቅቁ የኢትዮጵያ የቀውጢ ቀን አባላቱ የተለየ የክብር ቦታ ይሰጣል። በአኩሪ የትግል ታሪኩም ውስጥ አንፀባራቂ ኮከብ የሆነ ምዕራፍ ይኖራቸዋል። ድርጅቱም መቸም ቢሆን መቸ የሚረሳቸውና መዳረሻቸውን ከመጠየቅም ወደ

---


**EPRP**
**P.O.Box 73337**
**Washington D.C. 20056**
**U.S.A**
**Tel. : (202) 291-4217**
**Fax : (202) 291-7645**

**EPRP**
**BP 22**
**Bois Colombes 92270**
**France**

E-mail **ESPIC@aol.com** Website: **http://www.EPRP.com**

ኋላ የሚልበት ጊዜ አይመጣም:: የእነሱን ሁኔታ ማወቁ፤ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ መፈታታቸው ሁሌም ግንባር ቀደም ጥያቄያችን ይሆናል::

ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘረውና ሌሎቹም በወያኔ እጅ ወድቀው እስከዛሬ ድረስ መዳረሻቸው ያልታወቀው ጓዶቻችን፥ የት እንደወደቁ ትክክለኛውን እስክናውቅ ድረስ ማነኛውንም ጥረት ሁሉ ከማድረግ የማንቆጠብ መሆናችንን እያረጋገጥን፥ ማንኛቸውም የሰብዓዊ መብት መጣስ ተቆርቋሪ ድርጅቶችና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም የጓዶቻችንን መዳረሻ ለማወቅ በምናደርገው ፍለጋ እንዲተባበሩን ተማጽንዖችንን እናስተላልፋለን::

በወያኔ ጭካኔ ስር ወድቀው መዳረሻቸው የጠፋው የኢሕአፓ አባላት ስም ዝርዝር፡-

1. ፀጋየ ገብረመድኅን/ደብተራው/

2. አበራሽ በርታ

3. ስጦታው ሁሴን

4.--ይስሐቅ ደብረ ፅዮን
---------

5.--አምሀ በለጠ
------------

6.-ተክላይ ገብረ ሥላሴ----------

7.--ሀጎሰ በዛብህ

8. ታምራት-ግዛቸው

9. ሞት ባይኖር

10. ብርሃኑ እጅጉ

11. ለማ ኃይሉ

12. ተስፋዬ ከበደ

13. አበበ ዓይነ ኩሉ

14.ወንዱ ሲራክ ደስታ

15. ደምሴ ተስፋዬ

16. ዮሴፍ፤ አላዛርና ሌሎች በርካታ አባላት ናቸው ደብዛቸው:: የት ደረሱ ብለን መጠየቅና ደብዛቸውን ካጠፋው ጠላት ጋር መፋጠጥ ደግሞ ግዳጃችን ሆኖ ይቀጥላል::

ደብዛቸው የጠፋ ጓዶቻችን ሁኔታ ግልፅ ይሁን!!
የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ይፈቱ!!
ውድቀት ለወያኔ አገዛዝ!!!

**EPRP**
**P.O.Box 73337**
**Washington D.C. 20056**
**U.S.A**
**Tel. : (202) 291-4217**
**Fax : (202) 291-7645**

**EPRP**
**BP 22**
**Bois Colombes 92270**
**France**

E-mail **ESPIC@aol.com** Website: **http://www.EPRP.com**